የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDRAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ–ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th Year No. 31
ADDIS ABABA–4th July, 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፫/፲፱፻፺፬ ዓ·ም
የሕፃናት መብትና ደኅንነት የአፍሪካ ቻርተር
ማጽደቂያ አዋጅ ........................................ ገጽ ፩ሺ፰፻፳፱

## CONTENTS

Proclamation No. 283/2002
African Charter on the Rights and Welfare of the
Child Ratification Proclamation .............. Page 1829

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፫/፲፱፻፺፬
### የሕፃናት መብትና ደህንነትን በሚመለከት
### የወጣውን የአፍሪካ ቻርተር ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በ፳፮ኛው የመሪዎች ጉባዔ እ·ኤ·አ ጁላይ ፲፱፻፺ ያፀደቀውን የሕፃናት መብትና ደኅንነት በሚመለከት የወጣውን የአፍሪካ ቻርተር በሥራ ላይ ማዋል በማስፈለጉ፤

ቻርተሩ በሥራ ላይ የሚውለው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ፲፭ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል ሀገሮችን የቻርተሩ ማፅደቂያ ሰነዶች ከተቀበለበት ወይም የእነዚህ ሀገሮች ስምምነት ከተገኘበት ከ፴ ቀን በኋላ እንደሚሆን በቻርተሩ የተገለጸ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>
ይህ አዋጅ "የሕፃናት መብትና ደኅንነት የአፍሪካ ቻርተር ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፫/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ቻርተሩ ስለመጽደቁ</u>
የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባዔ እ·ኤ·አ· ጁላይ ፲፱፻፺ ባካሄደው ፳፮ኛው ስብሰባ የተቀበለው የሕፃናት መብትና ደኅንነት የአፍሪካ ቻርተር በዚህ አዋጅ ጸድቋል።

፫· <u>ቻርተሩን የማስፈጸም ሥልጣን</u>
የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህ የሕፃናት መብትና ደኅንነት የአፍሪካ ቻርተር በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>
ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም·

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

### *PROCLAMATION NO. 283/2002*
### *A PROCLAMATION TO RATIFY THE AFRICAN CHARTER ON THE RIGHTS AND WELFARE OF THE CHILD*

WHEREAS, it is necessary to implement the Charter adopted by the Assembly of Heads of States and Governments of the OAU at its twenty-sixth ordinary session held in July, 1990;

WHEREAS, it is stipulated in the Charter that the Charter shall come into force 30 days after the reception by the Secretary-General of the Organization of African Unity of the instruments of ratification or adherence of 15 (fifteen) member states of the organization of African Unity;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Charter at its session held on the 4th day of July, 2002;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as the "African Charter on the Rights and Welfare of the Child Ratification proclamation No. 283/2002"

2. *Ratification of the Charter*
The African Charter on the rights and Welfare of the Child adopted by the Assembly of Heads of State and Government of the OAU at its twenty-sixth ordinary session held in July, 1990, is ratified;

3. *Powers of the Ministry of Labour and Social Affairs*
The Ministry of Labour and Social Affairs is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Charter.

4. *Effective Date*
This Proclamation shall enter into force as of the 4th day of july, 2002.

Done at Addis Ababa, this 4th day of July, 2002.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80.001